# የ Family Day Care አስተማሪ እንደመሆንዎ፡-

## ሊያውቋቸው የሚገቡ ነገሮች



**AMHARIC**

ኖቬምበር 2018

Australian Government
Department of Education and Training

NSW FAMILY DAY CARE ASSOCIATION INC.

FAMILY DAY CARE EDUCATOR መሳሪያ :

# የ Family Day Care አስተማሪ እንደመሆንዎ፡- ሊያውቋቸው የሚገቡ ነገሮች

የ Family Day Care አስተማሪ ለመሆን የሚያስቡ ከሆነ ወይም እንዲሆኑ ጥያቄ ቀርቦሎት የሚያውቅ እንደሆነ ተተፈቀዱ የቅድመ ትምህርት እና ለትንንሽ ልጆች ቤትዎ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ እንክብካቤ ለመስጠት ይችሉ ዘንድ ሊያውቁዋቸው የሚያስፈልጉ ብዙ ቁልፍ ነገሮች አሉ።

የ Family Day Care ውስጥ በሚመዘገቡበት ወቅት ልጆችን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ፣ ለልጆች ትምህርታዊ ተሞክሮን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል፣ ጤና እና ደህንነት (ለእርሶ እና ለልጆች) እና የልጆች ጥበቃን በመሳሰሉ አካባቢዎች ላይሙሉ የሆነ የመግቢያ ስልጠና ሊሰጡዎት ይገባል።

አገልግሎትዎ ብቁ የሆኑ ቤተሰቦችን በመወከል የሚያስተዳድረውን የልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ በተመለከተ የቤተሰብ ድጋፍ ሕግን እንዲረዱ እና እንዲያከብሩ ሊያግዝዎ ይገባል።

ይህ በራሪ ወረቀት አስተማሪ ሆነው ከመጀመርዎ በፊት በሌሎች አካባቢዎች ላይ ማለትም እንደ - አስተዳደር፣ ክፍያዎች እና የመንግስት ድጎማዎች አይነት ሊያውቁዋቸው የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ያጠቃልላል። እንዳስተማሪ ሕጋዊ የሆነ ስራን ለመስራት እርዳታ ያደርግልዎታል። ለልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ ብቁ ሆነው ለሚገኙ ቤተሰቦች ለተለያዩ የልጆች እንክብካቤ ፍላጎቶች ወጪዎች ላይ ድጋፍ ያገኙ ዘንድ አስተዳደራዊ መስፈርቶቹ ምን እንደሆኑ እንዲረዱ እርዳታ ያደርግልዎታል። በተጨማሪም ከተመዘገቡበት የ Family Day Care አገልግሎት ምን መጠበቅ እንደሚችሉ እና እንዳለብዎት ያሳውቃል።

## ማጭበርበር እና Family Day Care

ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ የ Family Day Care በመስጠት ወቅት ወይም እንደሚሰጡ በሚያስመስሉበት ወቅት አስተማሪዎች ወይም Family Day Care ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ከአውስትራሊያ መንግስት ገንዘብ የሚያጭበረብሩበት ተደጋጋሚ የሆነ ክስተት ተፈጥሯል። ይህ በራሪ ወረቀት እርሶ ባለማወቅ ማጭበርበር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ለህጎች ያለመገዛት ባህሪ ውስጥ እንዳይገቡ ለማረጋገጥ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

## የ Family Day Care ክፍያዎች

የ Family Day Care የልጆች እንክብካቤ ወጪን ለመሸፈን ይሆን ዘንድ ክፍያዎችን ያስከፍላል። ይህ በእያንዳንዱ አገልግሎት ውስጥ የሚከናወንበት መንገድ ይለያያል - ቤተሰቦች ለአስተማሪዎች ክፍያዎዎችን በቀጥታ ወይም በአገልግሎቱ በኩል አስተማሪው ባንክ አካውንት ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ።

## የልጆች እንክብካቤ ድጎማ

የአውትራሊያ መንግስት ብቁ ሆነው ለሚገኙ ቤተሰቦች የልጆች እንክብካቤ ድጎማን የሚያደርገው የክፍያዎችን ዋጋ ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ ነው። የ Family Day Care አገልግሎቶች ቤተሰቦችን በመወከል ለህጻን እንክብካቤ ድጎማ ይቀበላሉ እናም በቅናሽ ክፍያ አማካኝነት ለቤተሰቦች ያስተካልፋሉ።

## ተጨማሪ የልጆች እንክብካቤ ድጎማ

ተጨማሪ የልጆች እንክብካቤ ድጎማ ለተለያዩ የቤተሰብ ሁኔታዎች ይከፈላል (ለምሳሌ፣ ጊዜያዊ የፋይናንስ ችግር፣ ወደ ሥራ ሽግግር፣ ለልጅ ደህንነት እና ዋና ተንከባካቢዎች ለሆኑ አያቶች)። በዚህ ምክንያት ለ Family Day Care አገልግሎትዎ ለቤተሰቦች ስለሰጧቸው የልጆች እንክብካቤ ትክክለኛ መረጃ ማቅረብዎ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም አገልግሎቱ ይህንን መረጃ ለልጆች እንክብካቤ ድጎማ እና ለተጨማሪ የልጆች እንክብካቤ ድጎማ አላማዎች ስለቀረበው የልጆች እንክብካቤ ለመንግስት ሪፖርት ለማድረግ ነው።

## ቁልፍ መመሪያዎች

የልጆች እንክብካቤ ድጎማ በቤተሰብ ድጋፍ ሕግ መሰረት ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች ለ Family Day Care አገልግሎቶች የሚከፈል ነው። ይህ ህግ የ Family Day Care አገልግሎቶች እና አስተማሪዎቻቸው የልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ በትክክል መከፈሉን ለማረጋገጥ መመሪያዎችን እንዲከተሉ ይጠይቃል።

የእነዚህ መመሪያዎች ምሳሌ ሊሆን የሚችለው፡-

- እያንዳንዱ ተማሪ ከእለታዊ እንክብካቤ ውስጥ በየእለቱ ሲወጣ እና ሲገባ ሊመዘገብ ያስፈልጋል። የ Family Day Care ሳምንታዊ የሰዓት መቆጣጠሪያ ማህደሮች ሊይዙ ያስፈልጋል ይህም ልጆች በየትኞቹ ቀናት እና ለምን ያክል ጊዜ እንክብካቤ እንዳገኙ ለማሳየት ነው። እነዚህ ማህደሮች አንድ የልጆች እንክብካቤ ድጎማ ክፍያ የተደረገለት ልጅ በተጠቀሰው ወቅት ላይ ያለውን አገልግሎት እንደተጠቀሰው እንዳገኘ ወይም ትክክለኛውን ምክንያት በተከተለ መልኩ ቀሪ እንደነበር ለማረጋገጥ ነው።
- የክፍለጊዜ ሪፖርቶች በሚፈለግበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመንግስት ሊላኩ ይገባል።
- ሁሉም ለቤተሰቦች የሚደረጉ ክፍያዎች በትክክል በደረሰኝ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ቤተሰቦች የልጆች እንክብካቤ ድጎማቸው ምን ያክል እንደነበር እና ተከፋይ በሆነው ሙሉ ክፍያ እና በድጎማቸው መካከል ካለው ልዩነት፣ በወጪ-መጋራት ምን ያክል እንደከፈሉ ማወቅ ይገባቸዋል።

## ድርጊትን ማሳወቅ

የተሳሳቱ ወይም ተገቢ ያልሆኑ ስነምግባሮች በመከሰት ላይ ናቸው የሚል ስጋት ካለዎት ለአውስትራሊያ መንግስት የትምህርትና የስልጠና ዲፓርትመንት ድርጊት ማሳወቂያ ከበቂ ዝርዝር ጋር በ 1800 664 231 ይደውሉ ወይም በ tipoffline@education.gov.au ኢሜል ይድርጉ። ከፈለጉ ማንነትዎን አለማሳወቅ ይችላሉ።



## አንድ ነገር ትክክለኛ ያልሆነ የሚመስልዎ ከሆነ፣ አያድርጉት!

ከህግ ተቃራኒ የሆነ የሚመስል ወይም የተሳሳተ የሚመስል ነገር ለማድረግ ሰው ጠይቶት ያውቃል? ይህም በሌላ አስተማሪ ወይም ቤተሰብ ውስጥ ባለ የ Family Day Care ሰጪ የሆነ ሰው ሊሆን ይችላል? የሚያጠራጥሮ ነገር ካለ፣ እየተጠየቁ ያሉት ነገር ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጡ። ኢሜይል info@fdcsupport.org.au በተጨማሪም የክልልዎን ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሊያገኙም ይችላሉ (ይህም ተማሪ ደህንነት ጋር ወይም ትምህርት ጋር የሚገናኝ እንደሆነ ነው) ለ ትምህርት እና ስልጠና ዲፓርትመንት በ www.acecqa.gov.au/help/contact-your-regulatory-authority ላይ ወይም ከክፍያ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ድግሞ በ 1800 664 231 ላይ ሊደውሉ ይችላሉ።

### ጠቃሚ ነጥቦች

- የ Family Day Care በተለያዩ ህጎች እና ደንቦች የሚሸፈን ነው።እነዚህም በስራ ላይ የዋሉት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-
  - ተማሪዎች ደህንነታቸው አስተማማኝ እንደሆነ እና በተንከባካቢ እንክብካቤ እንደሚያገኙ እርግጠኛ ለመሆን እና
  - የልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች በክፍያ ቅነሳ መልክ እንደሚሰጥ ለማረጋገጥ ነው።
- የ Family Day Care አስተማሪዎች በ Family Day Care አገልግሎት ውስጥ የተቀጠሩ ወይም በኮንትራክተርነት የተመዘገቡ ናቸው።
- ሕጎቹ እና መመሪያዎች እንዲሁም የ Family Day Care ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ቢዝነስዎን እንዴት እንደሚያንቀሳቅሱ ይቆጣጠራሉ።
- እነዚህ ህጎች/ደንቦች እና ፖሊሲዎች የሚከተለውን ይወስናሉ፡-
  - አገልግሎትዎ ክፍያዎችን እንዴት እንደሚወስን
  - ከአገልግሎቶችዎ ቤተሰቦች ምን ያክል እንደሚከፍሉ እና ምን አይነት ደረሰኝ እንደሚያገኙ
  - በምዝገባ ወቅት ምን አይነት መረጃ ሊገኝ እንደሚገባ
  - ስለተማሪዎች በሰዓት መገኘት ለ Family Day Care አገልግሎት ምን ዓይነት ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ እና ይህንንም በየምን ያክል ጊዜ ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ
  - ምን አይነት መድን ሊጠቀሙ እንደሚያስፈልግ
  - ተማሪዎችን ወደ ስርዓትዎ ለማስገባት እና ለማስወጣት ምን ዓይነት ስርዓቶችን በስራ ላይ ማዋል እንዳብዎ።
- የአውስትራሊያ መንግስት ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች የክፍያዎች መጠንን ለመቀነስ ይሆን ዘንድ የልጆች እንክብካቤ ድጎማ ይከፍላል። የ Family Day Care አስተማሪዎች ይህ ገንዘብ በትክክለኛ ቦታው ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለባቸው ይህንንም የሚያደርጉት፡
  - ወላጆች ልጆችን በሚያስገቡበት እና በሚያስወጡበት ወቅት ላይ በሰዓት መቆጣጠሪያ ማህደሮች ላይ ፊርማቸውን እንዲያስቀምጡ በማድረግ
  - የሚንከባከቡት ልጅ ወደ እንክብካቤ መስጫ በማይመጣ ወቅት ያለመገኘት ፊርማ በማስቀመጥ
  - የሰዓት መቆጣጠሪያ ማህደሮችን ለማስገባት አገልግሎታቸው ያስቀመጠውን መስፈርቶች በመከተል።
- ሕጉን መከተልዎን ለማረጋገጥ ማህደርዎ ትክክለኛ መሆን አለበት።
- የ Family Day Care አገልግሎቶች እነሱ ዘንድ ለተመዘገቡ አስተማሪዎች የተለያዩ ድጋፎችን ሊሰጡ ያስፈልጋል ይህም አስተዳደር በትክክለኛው እና ህጋዊ በሆነ መንገድ እየተከናወነ እንደሆነ ለማረጋገጥ እንዲሁም ተከታታይ እድገት የሚሰጥ እና ቀጣይ የሆነ ድጋፍ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ነው።
- ሕግ ሊጥስ ይችላል ብለው የሚያስቡት የ Family Day Care አገልግሎት ዘንድ አይመዝገቡ። ይህም ህግን የመጣስ ስጋት ውስጥ እርስዎን ሊከት ይችላል።
- የሚከተለውን አያድርጉ፡
  - እርሶ ካልሰጡት የቅድመ ትምህርት እና የልጆች እንክብካቤ ክፍለጊዜዎች አይፈርሙ
  - እርስዎ እንክብካቤ ካልሰጡ በስተቀር በተወሰኑ ቀናት ላይ ለተወሰኑ ልጆች አገልግሎት እንደሰጡ በሚያሳይ በማንኛውም ነገር ላይ አይፈርሙ
  - ለልጆቻቸው እንክብካቤ ያልሰጡ እንደሆነ ቤተሰቦችን ምንንም ነገር ላይ እንክብካቤ እንዲፈርሙ አይጠይቁ
- ፎርሞችን ወይንም ሌሎች ትክክለኛ ያልሆኑ ወረቀቶች ላይ የሚፈርሙ እንደሆነ ህግን መጣስ ነው።

### የልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ የሚሰራው እንዴት ነው?

የልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ ዓመታዊ የቤተሰብ ገቢን እና የእንቅስቃሴ ፈተና ግምገማን ጨምሮ አንድ ቤተሰብ ሁሉንም የብቁነት መመዘኛዎች በማሟላቱ ላይ የተመሰረተ ነው። በአጠቃላይ የልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች በክፍያ ቅነሳ መልክ እንዲተላከፍ በቀጥታ ለልጆች እንክብካቤ አገልግሎት ይከፈላል።

ቤተሰቦች በልጆች እንክብካቤ ድጎማ መጠን እና በሚከፈሉት ክፍያዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለአገልግሎት አቅራቢያቸው ይከፍላሉ። ለልጆች እንክብካቤ ድጎማ ብቁ ለመሆን፣ ቤተሰቦች ከልጆች እንክብካቤ አቅራቢው ጋር በገቡት ገዢ የጽሁፍ ዝግጅት ስር ያሉትን የልጆች እንክብካቤ ክፍያዎች የመክፈል ኃላፊነታቸውን መቀበል ይኖርባቸዋል።

FAMILY DAY CARE መሳሪያ

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

This brochure has been produced in 11 languages: Amharic, Arabic, Assyrian, Dari, Dinka, French, Hazaragi, Nuer, Somali, Sudanese, and Swahili. To find the brochure in your language please go to **www.fdcsupport.org.au**

## ወላጆች ልጆቻቸውን ሲያስገቡ እና ሲያወጡ በየእለቱ ፊርማቸውን እንዲያስቀምጡ ማድረግ የሚያስፈልገው ለምንድነው?

የሰዓት መቆጣጠሪያ ማህደሮች ሕጋዊ ሰነዶች ሲሆኑ የሚቀመጡትም የልጆች እንክብካቤ ድጎማውን ከአውስትራሊያ መንግስት የሚጠይቁ ቤተሰቦች በርግጥም የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት እንዳገኙ ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ነው።

## ለእኔ ድጋፍ ለመስጠት አገልግሎቴ ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

አገልግሎትዎ የሚከተለውን ሊያደርግ ያስፈልጋል፡

- እንዳስተማሪ ስራ ከመጀመርዎ በፊት የመግቢያ ስልጠና ሊሰጥዎ ይገባል
- ምን አይነት ክፍያ እንደሚያስከፍሉ ግልጽ ማድረግ
- ቀጣይ የሆነ ሙያዊ ማጎልበቻ እና ስልጠና መስጠት
- በየጊዜው እርስዎን መጎብኘት
- ብሄራዊ ሕግ እና ደንቦችን መረዳትዎን እና መከተልዎን እንዲሁም ብቁ የሆኑ ቤተሰቦችን ወክለው የሚያስተዳድሩትን የልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ በተመለከተ የቤተሰብ ድጋፍ ሕግን ማክበርዎን ማረጋገጥ።

## የተመዘገብኩበት አገልግሎት የማልገነዘባቸውን ነገሮች እንድፈርም ይጠይቁኛል። ይህንን ማድረግ ያስፈልገኛል?

በፍጹም። የሚፈርሙበትን ነገር በሙሉ እንደሚረዱ እርግጠኛ ይሁኑ አለዚያ ያለማወቅ ህግን በመጣስ ላይ ሊሆኑ ይችላሉ።

## የ Family Day Care ን የሚሸፍኑ ሕጎች እና መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

የ Family Day Care አቅራቢዎች፣ አገልግሎቶች እና አስተማሪዎች እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚቆጣጠሩ በርካታ ሕጎች አሉ። ወሳኝ የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፡

- **የትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ብሄራዊ ሕግ** www.acecqa.gov.au/national-law
- **የትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ብሄራዊ ደንብ** www.acecqa.gov.au/national-regulations
- **የቤተሰብ የድጋፍ ህግ፣** www.education.gov.au/child-care-legislation

## ብዙ ሕጎች እና መመሪያዎች ያሉት ለምንድን ነው?

ልጆችን መንከባከብ ወሳኝ የሆነ ስራ ነው። ብሄራዊው ሕግ እና መመሪያዎች ልጆች ደህንነታቸው አስተማማኝ ይሆን ዘንድ ለቅድመ ትምህርት እና ለልጆች እንክብካቤ ብሄራዊ መስፈርት ያስቀምጣል። የአውስትራሊያ መንግስት በልጆች እንክብካቤ ክፍያ ድጋፍ ላይ ብዙ ገንዘብ ያጠፋል። የቤተሰብ ድጋፍ ሕግ የልጆች እንክብካቤ ድጎማ እና ተጨማሪ የልጆች እንክብካቤ ድጎማ የቤተሰቦችን የልጆች እንክብካቤ ክፍያዎች መቀነስ እንዲችሉ መሰረት የሚጥል ነው።

## የበለጠ ይወቁ

የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ የመመሪያ መፅሐፍ ለቅድመ ትምህርት እና የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች በጣም አስፈላጊ የመረጃ ሐብት ነው እናም በሚከተሉት ላይ ማግኘት ይችላሉ፡
**www.education.gov.au/child-care-provider-handbook-0**
የበለጠ ለማወቅ ወደ እነዚህ ድረገጾች ይሂዱ፡

- **www.education.gov.au/compliance**
- **www.fdcsupport.org.au**
- **www.education.gov.au/child-care-providers**
- **www.fdca.com.au**
- **www.acecqa.gov.au**

ወይም በአቅራቢያዎ ወዳሉ የ Family Day Care አገልግሎቶች ይሂዱ። (በአቅራቢያዎ ያሉ አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ **www.fdca.com.au** ይሂዱና 'find childcare' የሚለውን ትር ጠቅ ያድርጉ።)

ኖቬምበር 2018

**Amharic** በራስዎ ቋንቋ በራሪ ወረቀት ለማግኘት **www.fdcsupport.org.au**. ድረ ገጽን ይመልከቱ

**Arabic** لإيجاد الكتيب بلغتك، يُرجى تصفح موقع الويب **www.fdcsupport.org.au**.

**Assyrian** [illegible] **www.fdcsupport.org.au**.

**Dari** برای دریافت جزوه به زبان خودتان، لطفاً به ویبسایت **www.fdcsupport.org.au** مراجعه کنید.

**Dinka** Të kɔɔr yin kitap në thoŋdu kitam tɔ̈ wëlthin ke yin lɔ në **www.fdcsupport.org.au**.

**French** Pour trouver la brochure dans votre langue, veuillez visiter le site **www.fdcsupport.org.au**.

**Nuer** Kɛ ɣöö bi ŋäc jiek rɛy warɛgakä/ kiɛ majalɛ kɛ thuok du, göa ɛ ɛn ɣöö bi wä kä **www.fdcsupport.org.au**.

**Hazaragi** برای دریافت این بروشور به زبان خود تان، لطفاً به ویب سایت **www.fdcsupport.org.au** مراجعه کنید.

**Somali** Si aad ugu heshid buugyaraha luuqadaada fadlan booqo **www.fdcsupport.org.au**.

**Sudanese** لإيجاد الكتيب بلغتك، الرجاء تصفح موقع **www.fdcsupport.org.au**.

**Swahili** Ili kupata brosha hiyo kwa lugha yako tafadhali tembelea tovuti **www.fdcsupport.org.au**.

Australian Government
Department of Education and Training

NSW FAMILY DAY CARE ASSOCIATION INC.
since 1976